አባሪ 1:- የበጀትና የወጪ አመላካቾች

አባሪ 1.1:- የ2013 በጀት ዓመት የገንዘብ ሚኒስቴር የወጪ መረጃ በፕሮግራሞች

መረጃ ሰጪው፡- ገንዘብ ሚኒስቴር

ዝርዝር	የወጪ ዕቅድ በሚሊ	እስከ2ኛሩብ ዓመት የወጣ	አፈፃፀም	ምርመራ
መደበኛ ወጪ				
ፕሮገራም አንድ	100.2	37.1	37.1%	
ፕሮገራም ሁለት	409.4	299.44	43.14%	
ፕሮገራም ሶስት	19.2	7.3	38.4%	
ፕሮገራም አራት	11.2	3.2	29%	
የመደበኛ ወጪ ድምር	540	347.04	64.25%	
የካፒታል ወጪ				
ፕሮገራም ሶስት(ኢፍሚስ)	400	100.3	25.1%	
ጥገና	80	43.2	54%	
የካፒታል ወጪ ድምር	480	143.5	29.8%	
ጠቅላላ ወጪ ድምር	1.02ቢሊዮን	490.5ሚሊዮን	48%	

መረጃውን የሞላው ስም ----ጌታቸው ከበሌ----

ፊርማ----[signature]---- ቀን----04/07/13----

መረጃውን ያረጋገጠው ስም----ግርማ መንግስቴ
የስትራቴጂክ ዕቅድና ሥራ አመራር
ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

ፊርማ----[signature]---- ቀን----

created with nitro PDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

1. የ2012 *የተቋሙ* በጀት አፈፃፀም

ለተቋሙ ለ2012 ለመደበኛ በጀት ዓመት ከትሬዥሪ ምንጭ የተስተካከለ በጀት 534 ሚሊዮን ብር፣ከውጭ ብድር 270 ሚሊዮን በድምሩ ብር 804 ሚሊዮን በጀት ተፈቅዷል፡፡ ለካፒታል በጀት ኢፍሚስ ፕሮጀክት ብር 338.2 ሚሊዮን እንዲሁም ለተቋሙ ለጥገና የተያዘ ብር 101.6 ሚሊዮን በድምሩ ብር 439.9 ሚሊዮን በጀት ተፈቅዷል፡፡

የአሥራ ሁለት ወራት የበጀት አጠቃቀምን በሚመለከት ከመንግሥት ግምጃ ቤት ለመደበኛ ወጭ ብር 514.2 ሚሊዮን ታቅዶ 282.8 ሚሊዮን (55 በመቶ) ሥራ ላይ ውሏል፡፡ ይህ የበጀት አጠቃቀም በፕሮግራሞች ሲታይ ለፕሮግራም አንድ ብር 127 ሚሊዮን ታቅዶ ብር 109 ሚሊዮን (85 በመቶ) ሥራ ላይ ውሏል፡፡ ይህም ከፍተኛ የሆነው በበጀት ዓመቱ በዕቅድ ያልተካተቱ ሥራዎች በመምጣታቸው፤ ለምሳሌ የውጭ ምንዛሬ መዋዥቅ ተጨማሪ ወጪ በማስከተሉ እና ሌሎች የሥራ ማስኬጃ ወጭዎች በመከፈላቸው ነው፡፡

ለፕሮግራም ሁለት ለመደበኛ በጀት ብር 377 ሚሊዮን ታቅዶ ብር 159.5 ሚሊዮን (42.31 በመቶ) ሥራ ላይ ውሏል፡፡ ይህ አፈፃፀም ያነሰበት ምክንያት ለዓለም አቀፍ መዋጮ ክፍያ በእቅድ የተያዘው ባለመከፈሉ ነው ለፕሮግራም ሦስት ለመደበኛ በጀት ብር 19.4 ሚሊዮን ታቅዶ 12.5 ሚሊዮን (64.43 በመቶ) ሥራ ላይ ውሏል፡፡ እንዲሁም ለፕሮግራም አራት ከመደበኛ በጀት ብር 10.5 ሚሊዮን ታቅዶ ብር 4.4 ሚሊዮን (41.9 በመቶ) ሥራ ላይ ውሏል፡፡ ለካፒታል በጀት (IFMIS ፕሮጀክት) ብር 338.2 ሚሊዮን በጀት ተይዞ በሥራ ላይ የዋለው ብር 265.5 ሚሊዮን (78.5 በመቶ) ሥራ ላይ ውሏል፡፡

2.የ2013 *የተቋሙ የበጀት* አፈፃፀም

ለተቋሙ ለ2013 ለመደበኛ በጀት ዓመት ከትሬዥሪ ምንጭ የተስተካከለ በጀት 1.02 ቢሊዮን ብር፣ ከውጭ ብድር 158 ሚሊዮን በድምሩ ብር 1.19 ቢሊዮን በጀት ተፈቅዷል፡፡ ለካፒታል በጀት ኢፍሚስ ፕሮጀክት ብር 400 ሚሊዮን እንዲሁም ለተቋሙ ጥገና የተያዘ ብር 80 ሚሊዮን በድምሩ ብር 480 ሚሊዮን በጀት ተፈቅዷል፡:

3. *የተቋሙ* የስድስት ወራት የበጀትአጠቃቀም

የስድስት ወራት የበጀት አጠቃቀምን በሚመለከት ከመንግሥት ግምጃ ቤት ለመደበኛ ወጭ ብር 540.08 ሚሊዮን ታቅዶ ብር 347. (64.2 በመቶ) ሥራ ላይ ውሏል፡፡

created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional

የበጀት አጠቃቀም በፕሮግራሞች በዝርዝር ሲታይ

- ለፕሮግራም አንድ ብር 100.2 ሚሊዮን ታቅዶ ብር 37.2 ሚሊዮን (37.1 በመቶ) ሥራ ላይ ውሏል፡፡
- ለፕሮግራም ሁለት ለመደበኛ በጀት ብር 409.4 ሚሊዮን ታቅዶ ብር 299.44 ሚሊዮን (73.14 በመቶ) ሥራ ላይ ውሏል፡፡
- ለፕሮግራም ሦስት ለመደበኛ በጀት ብር 19.2 ሚሊዮን ታቅዶ 7.3 ሚሊዮን (38.4 በመቶ) ሥራ ላይ ውሏል፡፡
- ለፕሮግራም አራት ከመደበኛ በጀት ብር 11.2 ሚሊዮን ታቅዶ ብር 3.2 ሚሊዮን (29 በመቶ) ሥራ ላይ ውሏል፡፡ ለካፒታል በጀት (IFMIS ፕሮጀክት) ብር 400 ሚሊዮን በጀት ተይዞ በሥራ ላይ የዋለው ብር 100.3 ሚሊዮን (25.1 በመቶ) ሥራ ላይ ውሏል፡፡ ለዚህ ዝቅተኛ አፈፃፀም ዋና ዋና ምክንያቶቹ የዳታ ማዕከል ግንባታ ስራ መጓተት፣የጥሪ ማዕከል ግንባታ አለመከናወን፣የቋሚና አላቂ ዕቃዎች እንዲሁም የአማካሪ ግዥዎችና ክፍያዎች በወቅቱ አለመከናወን ናቸው፡፡
- ለጥገና <u>80ሚሊዮን</u> ተፈቅዶ የኢፍሚስ መረጃ እንደሚያሳየን <u>43.2</u> ሚሊዮን(54ፐርሰንት) ስራ ላይ ውሏል፡፡

በአጠቃላይ በበጀት ዓመቱ ከመንግስት ግምጃቤተ ብር 1.02 ቢሊዮን በጀት ተይዞ በግማሽ ዓመቱ ብር 490.5 ሚሊዮን ወጪ በመፈጸም ከዓመቱ 48.08 በመቶ ወጪ ተፈጽሟል፡፡

created with nitroPDF professional
download the free trial online at nitropdf.com/professional